# ይነካል !

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ!

እግዚአብሔር ወልድ ይነካል። የሚነካውም በእምነት ነው! (ማቴ.9፥20-21፤ ሉቃ.8፥44)

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚሄድበት ሁሉ ብዛት ያላቸውና የተለያዩ ሰዎች ይከተሉት ነበር። 1ኛ) ከንግግሩ አጥምደው ሊወነጅሉት፥ ሊያጠፉት የሚፈልጉ (ጻሕፍት ፈሪሳውያን)፤ 2ኛ) ፈውስን የሚፈልጉ በሽተኞችና 3ኛ) አጃቢ (አጋፊ) በጌታ የሚሠራውን ድንቅና ተአምር ለማየት ለወሬ የሚከተሉ ነበሩ።

**ጌታን በእምነት መንካት** (ሉቃ.8፥44)

በአንድ ወቅት ኢያኢሮስ የሚባል የምኵራብ አለቃ (ክርስቶስን ሊያሳስሩት፥ ሊገድሉት ከሚፈልጉ ሰዎች ወገን መካከል የሆነ) ባለሥልጣን ወደ ኢየሱስ ቀርቦ በእግሩ ስር በመውደቅ ወደ ቤቱ ገብቶ ልትሞት የተቃረበች ልጁን እንዲያድንለት አጥብቆ ለመነ። (ሉቃ.8፥40-42)

እንኳን ተለምኖ ሳይለመን የሚገኘው አምላክ የምኵራብ አለቃውን ልመና ሰምቶ ወደ ቤቱ በሚሄድበት ጊዜ ከሕዝቡ ብዛት የተነሳ ግፊያና ጭንቅንቅ ነበር። በዚህም የጌታ መንገድ ላይ የምኵራብ አለቃው ልጅ ስትወለድ ደም መፍሰስ የጀመራት በሽተኛ ሴት በግፊያውና በትርምሱ ውስጥ ትገኝ ነበር። የምኵራቡ አለቃ ከኢየሱስ እግር ሥር በግንባሩ ተደፍቶ ልጁን በእጁ ዳስሶ ነክቶ ወይም በቃሉ ተናግሮ እንዲፈውስለት ወደ ቤቱ ሲለምን ይህቺ በሽተኛ ሴት ደግሞ በእምነት ተደፍታ "የጨርቁን ጫፍ ብነካ እፈወሳለሁ፥" እያለች በልቧ መሻት ነበር። (ሉቃ.8፥44) የምኵራቡ አለቃ በሚታየው እርሷ ደግሞ በማይታየው እምነት ግን ሁለቱም የክርስቶስን የፈውስ እጅ፥ ርኅሩኅ ልብ ፈልገው ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወደዚያ ሰፈር የመጣው ለምኩራብ አለቃው ሲል ቢሆንም ለነካችው የእምነት ሴትም ኃይልን ፈውስን ሰጠ። እርሱ ድንቅ አምላክ ነውና ለትልቁ ሄዶ ትንሹን አያልፍም። ይሰጠዋል። ለትንሹ ሄዶም ለትልቁ አይከለክልም። እርሱ የሚያየው ልብን እንጅ መልክን፥ ቁመናን ወይም ሥልጣንን አይደለም።

እኛም ብንሆን ከነዚህ ታሪኮች ትምህርትን በመውሰድ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደሚገኝበት ወደ ቤተክርስቲያን ስንመጣ አስቀድመን አመጣጣችን እንመርምር። ለሌሎች ፈውስ፥ ምሕረትና በረከት እንዲሆን በታላቁ አምላክ ፊት ልመና፥ ምልጃ ለማድረግ? ወይስ በእምነት እንፈወሳለን ብለን ለራስ ድነትና በረከት ፍለጋ? ወይስ ቦታ አጣባቢና አጋፊ በመሆን ፈውስ ፈልገው የመጡትን ደካማዎች ለመሸፈን፥ በረከት እንዳይደርሳቸው ለመከልከል ተመልካችና አዳናቂ ሆነን?

ሴትዮዋ ከቤቷ ይዛው ወደ እግዚአብሔር ወልድ የመጣችው የመዳን፥ የፈውስ እምነት በእምነት ይዛ ነው። ክርስቶስ እንደማያሳፍራት፥ እንዲሁ እንደማያልፋት፥ ሌሎቹን በሽተኞች ካደነ ከፈወሰ እርሷንም እንደሚፈዋሳት ተማምና ነበር። በመሆኑም ክርስቶስ ሆነ ቤተ ክርስቲያን ለሁሉም እኩል ናቸው። ለካህን፥ ለምዕመን፥ ለበሽተኛ ለጤነኛ፤ ለሕጻን ለአዋቂ የሚል አድልኦ የላቸውም። በውስጥዋ ተገኝተህ ጸልዩልኝ ከማለትህ በፊት ለራስህ በእምነት ጸልይ። እግዚአብሔር ቅርብ ነውና ላንተ የመጣ ኃይል ለሌላው በረከትና ፈውስ ይሆናል። እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ አምላክ ነውና ለሌላ የመጣው ፈውስ ደግሞ አንተን ዳስሶ ፈውሶና ባርኮ ያልፋል። ነገር ግን ከሁሉ አስቀድመህ የምትሄድበትን አላማ እና የምትለምነውን እወቅ። የተገኘህበት ሥፍራም ቅዱስ እግዚአብሔር እንዳለበት እወቅ። መገኘትህም በመፍራት፥ በመንቀጥቀጥ፥ በአክብሮትና በእምነትም ይሁን።

**ጌታን በእይታ መንካት** (ሉቃ.19፥1-10)

በወንጌል የተተረከ ዘኬዎስ የሚባል ኃጢአተኛና የቀራጮች አለቃ ነበር። ይህ ሰው ክርስቶስን ሊያይ ፈልጎ ከሕዝቡ ብዛት የተነሳ አልቻለም። በቁመቱም አጭር በመሆኑና ሥፍራው ሁሉ በአጋፊ መጣበብ የራሱ የሆነ የግል ቦታ እንዲፈልግ ግድ ሆነበት። ከሕዝቡ ጭንንቅ ፊትም ነጥልና ገንጠል ብሎ ጌታን የሚያነጋግርበት ሳይሆን በዓይኑ እንኳን የሚያይበትን የራሱ የሆነ

መንገድ አዘጋጀ። ከአንዲት የሾላ ዛፍ ላይም ተንጠላሎ በግፊው፥ በትርምሱ መካከል ጌታን በልቡ በመሻት በዓይኖቹም ይፈልገው ጀመር።

ኢየሱስም የዘኬዎስን ልብ አይቶ ወደተንጠላጠለባት ዛፍ ሄደ። አሻቅቦም አይቶ፥ በስሙ በመጥራት፥ "ዘኬዎስ ሆይ፥ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ" አለው።

ዘኬዎስም ከዛፉ ፈጥኖ እንደ ወረደ ጌታ በደስታ ተቀበለው። ዘኪዎስም በኃጢአተኛነቱና በቀራጭነቱ አምላክን ሳያውቅ፥ በሕይወቱ የኖረበት ዘመን ከሾላ ዛፍ ላይ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ትርጉም ዐልባ ነበር። የሚያስደንቀው ነገር ክርስቶስ መንፈሳዊ ዓይኖቹን ሲከፍት፥ "ጌታ ሆይ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ። ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ፥" ብሎ በፊቱ ቃል ገባ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለዘኬዎስ ቤት መዳን ሆነለት። ታሪኩም ተቀየረ። (ሉቃ.19፥1-10)

እንግዲህ እኛም እንደ ዘኬዎስ ከአጋፊ ለየትና ነጠል ብለን ክርስቶስን በልባችንም በዓይኖቻችንም እንፈልገው። የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ወልድ በእኛ ሕይወት ይገለጣል። የእግዚአብሔር ክብር ወደ እኛ ሲመጣና ሲገኝም ዘኬዎስ የሠራው ኃጢአትና በደሉ ቁልጭ ብሎ በግልጽ እንደታየው ለእኛም በደላችን ይታወቀናል። ሁሉን የሚያይ፥ ሁሉን የሚያውቅ፥ ሁሉን የሚሰማ ጌታ በሚፈለግበት ቦታ ሁሉ የሚገኝ ነውና እውነተኛው ንስሐ በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ እናገኛለን።

ዛሬ ጌታ ወደ ቤታችን መጥቶ ሊጋበዝ፥ በበር ቆሞ እየቆረቆረ ስለሆነ እንስማው ዘንድ ጊዜና ጆሮአችንን እንስጠው። ሰምተንም እንክፈትለት። ጌታ በቤታችን በልባችን ተገኝቶም እውነትን፥ ኃጢአታችንንና በደላችን ሲገልጥም ለንስሐ እንዘጋጅ። ነገር ግን በኃጢአት መውደቅ ብቻ ሳይሆን እየኖርን እንዳንሆን ቁርቁራውን ለመስማትና ለማዳመጥ የጥድፊያና የወከባ ሕይወትን አንምረጥ።

ክርስቲያኖች ምዕመናንና ምዕመናት ሆይ፥ የመዳን ቀን ዛሬ ነውና ጌታን ፍለጋ እንደ ምኵራብ አለቃው በአካል ተገኝተን፤ ደም ይፈሳት እንደነበረችው ሴት በእምነት "ጨርቁን ብዳስስ እድናለሁ፥" ብለን፤ እንደ ዘኬዎስም ዛፍ ላይ ተንጠልጥለን በእምነት መሻት ጌታን እንቅረበው። መዳን ለቤታችን ይሆንልናል።

**ጌታን በጩኸት መንካት** (ማር.10፥45-52)

በርጤሜዎስ የተባለ ዓይነ ስውር በመንገድ ዳር ተቀምጦ ሲለምን ማየት ባይችልም ጫጫታና ግርግር እንዲሁም የትርምስ ድምጽ ይሰማ ነበር። ለግርግሩ፥ ለትርምሱና ለጫጫታው ምክንያት የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ እንደ ሆነ ባወቀም ጊዜ ድምጹን ከፍ አድርጎ፥ "የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ማረኝ" እያለ ይጮኽ ጀመር።

ብዙ አጋፊዎችና አጨናናቂዎች ግን ወደ ኢየሱስ እንዳይቀርብ፥ እንዳይጠጋ አርፎ እንዲለምን ገሡጹት። በዓይነ ስውርነቱ ፀንቶ ለማኝ ሆኖ እንዲኖር የሚፈልጉ አጋፊዎችም ዝም እንዲል ያላደርጉት ጥረት አልነበረም። እጃቸው

የማይፈታውና የማይሰጡት ፈሪሳውያን እንኳን ሳይቀሩ አፉን መሸበቢያ ገንዘብ ሳይሰጡት አልቀሩም። በርጤሜዎስ ግን ማየትን መርጦ ብርሃንን ፈልጓልና፥ "የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ" እያለ ደጋግሞና አብዝቶ ጮኸ።

ጌታም ጩኸቱን ሰምቶ ቆመና፥ "ጥሩት" አለ። ያን ጊዜ "ዝም በል" ብለው የገሠጹት ያሉት ሁሉ መርዳት ጀመሩ። በርጤሜዎስም እንደመጣ፥ ጌታ፥ "ምን ላደርግልህ ትወዳለህ?" ብሎ ጠየቀው

እርሱም፥ "መምህር ሆይ፥ አይ ዘንድ" ብሎ መለሰ።

ኢየሱስም፥ "ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል፥" አለው። (ማር.10፥45-52)

ከታሪኩ እንደምንረዳው ኢየሱስ በጩኸትም ይነካልና በጉርጓድ በጨለማ ውስጥ ያለን፤ ነገሮች ያልተስተካከሉልን፤ ቀናት የከፉብን ሁሉ አብዝተን ወደ ኢየሱስ እንጨኽ። ጌታ ባልታሰበው ጊዜ ድንገት ይደርስልናል። ብርሃን ይሆንልንና ጨለማውም ይሸሻል። ጠማማ ሁሉ ይቀናል። ጠላቶችም ወዳጅ ይሆናሉ።

የዘለዓለም አምላክ ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለያዩ መንገዶች በግል፥ በጩኸት፥ በልመና፥ በምልጃ፥ በመሻት፥ በእይታ ወ.ዘ.ተ መንካትና መፈወስ ይቻላል። ዛሬ እኛ በቤተ ክርስቲያን መገኘታችን ልምድ ሆኖብን በአንተ፥ በአንቺና እኔ ምክንያት ኢየሱስ ለሚፈልጉት የተሸፈነ እንዳይሆን፥ እንጠንቀቅ። ቀድመን በመገኘትም ቦታ ይዘን በማጣበብ አጋፊ ሆነንም መዳን ለሚሹት ፈውስ እንዳይሆን፥ በረከት እንዳይመጣ፥ ቸርነት እንዳይከሰት ከልካይ እንዳንሆን እናስተውል። የእምነትን ነገር በልባችን ሳይሆን በአፋችን ይዘን፥ ወንበር ላይ በመቀመጥ ቅድስትን ሞልተን አጨናንቀን ከዐውደ ምሕረት የሚመጣውን ፈውስ፥ ምሕረትና በረከት ወደሌሎች፥ ወደሚፈልጉት እንዳይደርስ እንደ አጥር ሸፍነን እንዳንይዝ እግዚአብሔር ያስተምረን። ከዚህም መሰናክልነት፥ የወንድም የእኅት እንቅፋት ከመሆን ያድነን። ከግርዶሽ ያውጣን! በእኛ ምክንያትም እግዚአብሔር እንዳይሸፈን፥ አጋፊዎች ሳንሆን በአንተ፥ በአንቺ፥ በእኔ በሁላችን ሕይወት ጌታ እንዲታይና ለፈውስ፥ ለምህረት እንዲነካ ይሁን። ለእኛም ለራሳችን ምህረት፥ ፈውስና ቸርነት እንዲሆንልን ክርስቶስን በእምነት እንንካው እንጂ አናጋፋው።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ይነካል!"

ይነካል (ጠብቆ)፦ አምላክ ነውና መንፈስ ቢሆንም ቅሉ በእጅ ይነካል፥ ይዳሰሳል። ለልባችን የቀረበ አምላክ ነው።

ይነካል (ላልቶ)፦ አዎን ሕያው አምላክ ነውና በፍቅሩ፥ በመንፈሱ፥ በቃሉ፥ በትኅትናው፥ በምሕረቱ፥ በቸርነቱ፥ በፈውሱ ወዘተ… ይነካል።…

ስብሐት ለእግዚአብሔር!
፪ሺ፫ ዓ.ም.
የእግዚአብሔር አገልጋይ
መ.ሙላት